የኢትዮጵያን ከፍታ ጠቋሚዎች

(“BBC” እንደመነሻ)

ስሜነህ

የኢንዱስትሪ ዘርፍ እጅግ በላቀ ፍጥነት ማደግ አለበት። ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ የተሃድሶ መስመር ወደ ሁለተኛውና ሶስተኛው የእድገት ምእራፎች የሚደረገው ጉዞ ኢንዱስትሪውን ይዞ እንደሆነ ያመለክታል። የአገራችን ኢንዱስትሪ ዘርፍ በፍጥነት ማሳደግ በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ እመርታዊ ለውጥ በማስመዝገብ ኢኮኖሚያዊ የመዋቅር ሽግግር መፍጠር የእድገቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሁኔታ ነው። ወደ ኢንዱስትራላይዜሽን የሚደረገው ሽግግር ምኞት ሆኖ እንዳይቀር አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተሰርተዋል፤ እየተሰሩም ነው።

አንደኛው የመሠረተ ልማት አቅርቦት በጥራትና በርካሽ ማቅረብና ማሟላት ነው። ይህ ተግባር ከሞላ ጎደል ተፈፅሟል። ሁለተኛው የሰለጠነ የሰው ሃይል በበቂ ማልማትና ማቅረብ ነው - ይህም ተግባር ከሞላ ጎደል ተፈፅሟል፤ በመፈፀም ላይ ነው። ሶስተኛው የፋይንናስ አቅርቦትና የአሰጣጡ ፍትሃዊነት ማረጋገጥ ሲሆን በዚህ አቅጣጫም የተሻለ መጓዝ ተችሏል። በኢንዱስትራላይዜሽን ዘርፉ በዋናነት የሚታየው የመሬትና የመስሪያ አቅርቦት ችግሮችን ለመፍታት የኢንዱስትሪ ዞኖችን የመከለልና የኢንዱስትሪ ፓርኮችና ክላስተሮችን የመፍጠር ጉዳይ ነው። ይህም ተግባር እየተፈፀመ ይገኛል። እነዚህን ሁኔታዎች በደምሳሳው ስናያቸው ሂደቱና ሽግግሩ በአስተማማኝ መስመር ላይ መሆናቸውን ያመለክታል። አብነቶች እናንሳ።

በድሬደዋ በ47ሚሊዮን ብር የተገነባው የፋብሪካ እቃዎች መለዋወጫ ማምረቻ ተቋም ሥራ ለማጀመር ዝግጅቱን ሁሉ አጠናቋል። በአስተዳደሩና በመከላከያ ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ትብብር የተገነባው ይህ ተቋም በ2007 ዓ.ም የተጀመረና በቅርቡ የተጠናቀቀ ሲሆን፤ ተቋሙ ከእህል ወፍጮ እስከ ከፍተኛ ፋብሪካ የሚያገለግሉ መለዋወጫዎች በማምረት ከውጭ ለማስገባት ይወጣ የነበረውን የውጭ ምንዛሬ ለማስቀረትና የኢንዱስትሪ ሽግግሩን ለማፋጠን አስተዋጽኦው የላቀ እንደሆነ በባለሙያዎች የተመሰከረለት ነው።

የማምረት ስራውን በቅርቡ በሚጀምረው በዚህ የኢንዱስትሪ ተቋም ወደ ስራ የሚሰማሩ ወጣቶች በአክሲዮን ማህበር ተደራጅተው የሚሰማሩ ይሆናል። የብድር አገልግሎት በአስተዳደሩ የሚመቻችላቸው እነዚህ ወጣቶች ለማሽን ግዥ የወጣውን ወጭ ሲመልሱ ማምረቻው ወደማህበራቸው ይዘዋወርላቸዋል። ለዚህም ወጣቶቹን አደራጅቶ ከባንክ ጋር የማስተሳሰሩ ስራ ከሞላ ጎደል ተጠናቋል።

ይህን እንደአብነት ማንሳታችን በኢንዱስትሪው መስክ የኢትዮጵያ ከፍታ በመረጋገጥ ላይ መሆኑን የተመለከተ ዘገባ ከወደቢቢሲ በመሰማቱ ነው።

ቢቢሲ በቴሌቪዥን ጣቢያው ኢትዮጵያ የአፍሪካ ቀዳሚ የማኑፋክቸሪንግ ማዕከል መሆን ትችላለች በሚል ርዕስ ነው ዘገባውን ያሰራጨው። በሃገሪቱ እየታየ ያለውን እድገት በምስል አስደግፎ ያቀረበው ቢቢሲ የሐዋሳ ኢንደስትሪያል ፓርክን ለአብነት በዘገባው አካቷል። የሐዋሳ ኢንደስትሪ ፓርክ ስራ ከጀመረ ስድስት ወራት እንደተቆጠረ ያስታወቀው ዘገባው የኢንዱስትሪ ፓርኩ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ ወዲህ ለአስር ሺህ ሰዎች የስራ ዕድል መፍጠሩን እና በሙሉ አቅሙ መስራት ሲጀምርም ለ60ሺህ ሰዎች የስራ ዕድል ይፈጥራል ተብሎ እንደሚጠበቅ አመላክቷል።

በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች የኢንዱስትሪ ፓርኮች በመገንባት ላይ እንደሚገኙ የሚዘረዝረው የቢቢሲ ዘገባ በዓለም ምርጥ የተባለውን የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የመገንባት እና የማስፋፋት ሞዴልን ስለመምረጣችንም አውስቶልናል። ኢትዮጵያ የወደፊቱን ነው በመገንባት ላይ የምትገኘው ሲል ያወደሰው ዘገባው የግንባታው መጠን እና ተስፋ ደግሞ አስደናቂ መሆኑን፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ብቻ ሳይሆኑ ዋጋቸው ተመጣጣኝ የሆኑ የመኖሪያ ህንጻዎች በመገንባት ላይ እንደሚገኙ እና የመንገዶች ግንባታ እንዲሁም ሀገሪቷን ከጅቡቲ የሚያገናኝ በኤሌክትሪክ ሀይል የሚሰራ የባቡር መንገድ ተገንብቶ ወደ ስራ በመግባት ላይ መሆኑን በምስል አስደግፎ አቅርቧል።

የሃዋሳ ኢንዱስትሪ መንደር ሃያ ዓለም አቀፍና የአገር ውስጥ የጨርቃ ጨርቅና የአልባሳት አምራች ፋብሪካዎችን የያዘ ነው። ፓርኩ ለአምራቾች የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲሰጡ የታሰቡ የአንድ መስኮት አገልግሎቶች የተሟሉለት ሲሆን፣ ዋና ዋናዎቹም የኤሌክትሪክ፣ የውኃ፣ የስልክ፣ የሎጂስቲክስ፣ የጉምሩክ፣ እንዲሁም የቪዛ አገልግሎትን ያካተተ፤ በጥቅሉ ውጣውረድ ያልበዛበትና የኪራይ ሰብሳቢ ቢሮክራቶችን ቀዳዳዎች ሁሉ የሚደፍን አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ነው፡፡

በዚህ መንደር በዘርፉ ዓለም አቀፍ ዝና ያላቸው 14 የጨርቃ ጨርቅ አምራቾች ስራቸውን ጀምረዋል። ከእነዚህ ውስጥም የ130 ዓመታት ልምድ እንዳለው የሚነገርለት የአሜሪካው ፒቪኤች ይገኝበታል። የበርካታ አመታት ልምድ ያለው ፒቪኤች ካልቪን ክሌይ፣ ቶሚ ሂል ፊገርና በመሳሰሉት የአልባሳት መለያዎች (ብራንዶች) ይታወቃል። የቻይናው ውሺ ጂንማኦ፣ የህንዱ አርቪንድ የመሳሰሉትን ጨምሮ የሆንግ ኮንግ፣ የቤልጂየም፣ የሲሪላንካና የአሜሪካ ኩባንያዎች ስንቅና ትጥቃቸውን አሟልተው በመንደሩ ከከተሙ ወራት ተቆጥረዋል። በእነዚህም ወራት መጪው ጊዜ የኢትዮጵያ ከፍታ መሆኑን የሚያጠይቁ ስራዎችን እያከናወኑ መሆኑን ከቢቢሲ ዘገባ ለመገመት አይከብድም።

በሃዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገኙት የአገር ውስጥ ኩባንያዎች ስድስት ሲሆኑ፣ ስለኢትዮጵያ ከፍታ አቅማቸውንና ተሳትፎአቸውን ለማሳደግ ከመንግሥት ልዩ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፤ እየተደረገላቸውም ነው። ስለዚሁ ከፍታ በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ ገብተው ለሚሳተፉ ባለሀብቶች መንግሥት እስከ 85 በመቶ የሚደርስ የባንክ ብድር አመቻችቷል። ይህ ግዙፍ የኢንዱስትሪ ፓርክ በመቐለ እና ኮምቦልቻ ለተጀመሩት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታ በሰአቱ መጠናቀቅ የላቀ ልምድ የተቀመረበት እነደመሆኑ ለቀጣዩ ጉዞም የጎበጡ መንገዶችን ሁሉ ያቀና ፓርክ ነው።

ፓርኮቻችን በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ብቻ የታጠሩ አይደለም። በተለይ በስትራቴጂው ላይ ልዩ ትኩረት በተሰጠው የአግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍም ፓርኮቻችን መዝለቃቸው የደረስንበትን ደረጃና መጪው ዘመን የኢትዮጵያ ከፍታ መሆኑን የሚያጠይቁ ናቸው።

በአግሮ-ፕሮሰሲንግ ዘርፍ በነጠላ ከሚደረግ መፍጨርጨር እየተወጣና በፓርኮች ደረጃ መፈጸም ወደሚያስችሉ አግባቦች እያመራን ለመሆኑ በርከት ያሉ አስረጂዎች መጥቀስ ይቻላል። ከአስረጂዎቹ ሁሉ የሚልቀውና ሚዛን የሚደፋው ደግሞ በመጪው ጥር ግንባታቸው የሚጀመረውና የአገሪቱን የኢኮኖሚ ሽግግር እንደሚያፋጥኑ የሚጠበቁት የተቀናጀ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ናቸው። ፓርኮቹ የግብርና ምርት የሚያቀነባብሩ ፋብሪካዎች ማዕከል የሚሆኑ ሲሆን፤ የፓርኮቹ ግንባታ በአማራ¬-ቡሬ፣ በትግራይ-ሁመራ፣ በኦሮሚያ¬-ቡሌቡላ አካባቢና በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች¬ - በሃዋሳ አካባቢ የሚከናወኑ ናቸው።

የፓርኮቹ መገንባት የግብርናውን ምርት የእሴት ሰንሰለት በማጠናከር በዘርፉ የተሰማሩ ባለኃብቶችንና አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ከማድረግ ባለፈ የአገሪቱን የኢኮኖሚ ሽግግር በማፋጠን የኢትዮጵያን ከፍታ የሚያረጋግጡ እንደሚሆን አያከራክርም። በአገሪቱ በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነው ፕሮጀክት በአዲስ አበባ ዙሪያ ተወስኖ የነበረውን የኢንዱስትሪ ፓርክ ግንባታ ወደ ክልሎች በማስፋትም በከተሞች ለሚከናወነው የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ እንደሚሆን መገመት አይከብድም።

የኢንዱስትሪ ፓርኮቹን ለመገንባት በሁሉም ክልሎች 17 የግብርና ቀጣናዎች የተለዩ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ አራቱ ፓርኮች በሚቀጥሉት አራት ዓመታት ግንባታቸው ተጠናቆ ወደ ሥራ እንደሚገቡ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የወጡ መረጃዎች ያመለክታሉ።

የፓርኮቹ መገንባት አገሪቱን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለማሰለፍ እና ኢንዱስትሪው አሁን ካለበት 15 በመቶ ወደ 28 በመቶ ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት ለማሳካት ከፍተኛ ድርሻ የሚኖረው መሆኑም ነው በኢንዱስትሪው ዘርፍ መጪው ዘመን የኢትዮጵያ ከፍታ የሚረጋገጥበት እንደሆነ የሚያጠይቀው።